AASTU

UNIVERSITY FOR INDUSTRY

መስከረም 24 ቀን 2018 ዓ.ም.

## በ2018 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የቅድመ ምረቃ መደበኛ አዲስ ገቢ ተማሪዎች ለሆናችሁ በሙሉ

የ2017 ዓ.ም. የ12ኛ ክፍል ፈተና ተፈትናችሁ፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን የመጀመሪያ ምርጫችሁ ሳደረጋችሁ እና የመግቢያ ፈተናውን አልፋችሁ በዩኒቨርሲቲያችን በ2018 ዓ.ም ለተመደባችሁ የቅድመ ምረቃ መደበኛ አዲስ ገቢ ተማሪዎች እንኳን ደስ አላችሁ። **<u>ወደ ዩኒቨርሲቲያችን በአካል ቀርባችሁ ሪፖርት የምታደርጉበት ቀን ሰኞ ጥቅምት 03/2018 ዓ.ም</u>** መሆኑን አውቃችሁ ሪፖርት እንድታደርጉ ዩኒቨርሲቲያችን ጥሪውን ያቀርባል።

**ማሳሰቢያ፡**

1. ወደተቋማችን ስትመጡ ብርድልብስ፣ አንሶላ፣ የትራስ ጨርቅ እና የስፖርት ትጥቅ ይዛችሁ መምጣት ይኖርባችኋል።
2. ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መረጃዎች
    - 2.1. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ውጤት ሰርተፊኬት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
    - 2.2. ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ትራንስክሪፕት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
    - 2.3. የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ውጤት ሰርተፊኬት ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ፣
    - 2.4. አራት 3በ4 ፎቶግራፍ
3. ከተጠቀሰው ቀን ቀድሞም ሆነ ዘግይቶ የሚመጣ ተማሪ የማናስተናግድ መሆኑን ከወዲሁ እናሳውቃለን።
4. የተማሪዎች የመኝታ (ዶርሚቶሪ) ህንፃ እና ክፍል፣ የመማሪያ ክፍል፣ የዩኒቨርሲቲ ኢ-ሜይል አድራሻ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ መለያ ቁጥር (ID No) ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በቅርቡ የምናሳውቅ ሲሆን የዩኒቨርስቲያችንን ማኀበራዊ ድረ ገጾች እና በይነመረብ እንድትከታተሉ እንጋብዛለን።

**እንኳን ወደ አዲስ አበባ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በሰላም መጣችሁ። ዩኒቨርሲቲ ለኢንዱስትሪ!**

**የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር እና አሉምናይ ዳይሬክቶሬት**